# የራስ አገዝ ቡድን አሰራርን በኮቪድ-19 ወቅት ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለመስራት የወጣ መመሪያ

በራስ አገዝ ቡድን አሰራር ድርጅቶች ህብረት በኢትዮጵያ

**ተዘጋጅቶ የቀረበ**

2012 ዓ.ም|አዲስ አበባ

# መግቢያ

የራስ አገዝ ቡድን አሰራር አላማ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችን በተለይም ሴቶችን በዘላቂነት ከድህነት ለማውጣት የሚተገበር አሰራር ነው፡፡ አሰራሩ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶች በኢኮኖሚ፣ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፎች በማብቃት በራሳቸው፣ በቤተሰባቸው እንዲሁም በአካባቢያቸው ላይ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ያግዛል፡፡በሶስቱ የራስ አገዝ ቡድን አሰራር ደራጃዎች ማለትም የራስ አገዝ ቡድን፣ህብረት እና ጥምረት ውስጥ የሚሳተፉ አባላት በአካባቢያቸው ከሚገኙ ሀብቶች ተጠቃሚ ለመሆን እድል ይፈጠርላቸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኮሳፕ አባል ድርጅቶች አስተባባሪነት ከ233 ሺ በላይ ሴቶች በ12 ሺ ቡድኖች ውስጥ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ የራስ አገዝ ቡድን አባላት በሳምንታዊ ቁጠባቸው እና ከቡድን በሚወስዱት ብድር የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ በመሳተፍ ገቢያቸውን በማሻሻል የኢኮኖሚ ለውጦችን አምጥተዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የቡድን አባላት የተሻለ የምግብ አቅርቦት ማግኘት እና ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ችለዋል፡፡በተጨማሪም የራስ አገዝ ቡድን አባላት በቤተሰባቸው እና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ተሳትፎአቸውን በመጨመር በራሳቸው እና ቤተሰባቸውን ብሎም ማህበረሰባቸው በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሰጪነት ሚናን በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡የራስ አገዝ ቡድን አባላት በህብረት ውስጥ አከባቢያቸውን እና ማህበረሰባቸውን ምቹ እና የተሻለ የማድረግ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በኮረና ቫይረስ ስርጭት ለመግታት በተወሰዱ እርምጃዎች ምክንያት መደበኛ የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት እና አባላት ተጽኖ ደርሶባቸዋል፡፡የቡድኖች ሳምንታዊ ስብሰባ ፣ሳምንታዊ ቁጠባ ፣የአባላት ገቢ ማስገኛ ስራዎች በምሳሌኔት ማሳት ይቻላል፡፡በተጨማሪም የቡድን አባላት የእለት ገቢያቸውን በተለመደው መልኩ ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮባቸዋል፡፡በመሆኑም በራስ አገዝ ቡድን አሰራር ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ይህን ወቅት የሚሻገሩበትን መንገድ በጋራ በመሆን መፈለግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የመመሪያው ዓላማ

ድህነትን በመፋለም እና ማህበረሰብን የተሻለ በማድረግ ጥረት ውስጥ የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት(ህዝባዊ ተቋማት) የፅናት እና የጥንካሬ ተምሳሌት ሆነው ይወሳሉ፡፡ እነዚህ ተቋማት በአካባቢያቸው በጎ ተጽዕኖን በማምጣት የሚታወቁ፣ከባለድርሻ አካላት ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላቸው እንዲሁም በአካባቢያቸው ያለውን ሀብት በማሰባሰብ የመሰረተ ልማት እንዲሁም ሌሎች ችግሮችን የመፍታት ልምድ እንዳለቸው ይታወቃል፡፡ከኮቪድ -19 ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የመደበኛ የኑሮ ሁኔታ ለውጦች በሚቀጥሉት ወራት እንደሚቀጥሉ የአለም ጤና ድርጅት ሪፖርቶች ያመላክታሉ፡፡በመሆኑም ከራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ጋር የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት እንደ ልማት ሰራተኞች ይህንን ከባድ ወቅት የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ተቋቁመው የሚያልፉበተን መንገድ መፈለግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ይህ መመሪያ የራስ አገዝ ቡድን አሰራር ላይ ለሚሰሩ አካላት የራስ አገዝ ቡደን ተቋማት በኮቪድ19 ወቅት ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ማካሄድ የሚቻልበትን መንገዶች ያመላክታል፡፡

# ክፍል አንድ፤
# መሰረታዊ መርህ

### ቅድሚያ ለደህንነት

ማንኛውም የራስ አገዝ ቡድን ተቋም ተግባር በሚከናወንበት ወቅት፣ የአለም ጤና ድርጅት፣የጤና ሚኒስቴር ፣የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እንዲሁም የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት የሚገኙበት የክልል መስተዳደሮች የሚያወጡትን ደንብ እና መመሪያዎች በተከተለ መልኩ መሆን  አለበት፡፡

# ክፍል ሁለት፤
# የራስ አገዝ ቡድን አሰራርን ለሚያስተባብሩ ድርጅቶች መመሪያ

የራስ አገዝ ቡድን አሰራርን የሚያስተባብሩ ድርጅቶች ፤የራስ አገዝ ቡድን ተቋማትን በኮቪድ-19 ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ተቋማቱን በማገዝ የመሪነት ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤

### የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ለመደገፍ ቁርጠኝነትን በተግባር ማሳየት

- የድርጅቱ አመራሮች ማለትም ዳይሬክተሮች እና የፕሮግራም አስተባበሪዎች የራስ አገዝ ቡድን ተቋማትን ለመደገፍ ሰራተኞችን መመደብ፣ አቅጣጫ መስጠት፣በጀት መመደብ
- የፕሮጀክት ሰራተኞች የራስ አገዝ ቡድን አሰራር ስራዎችን መምራት ይህም አመቻቾችን ማስተባበር፣ለራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ
- አመቻቾች ወቅታዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ለራስ አገዝ ቡድን ተቋማት የቅርብ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ

### የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት በኮቪድ-19ን ተቋቁሞ ለማለፍ የሚያስችል ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ማገዝ

- የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት መደበኛ ተግባሮችን(ሳምንታዊ ስብሰባ፣ቁጠባ፣ ብድር መመለስ የመሳሰሉት) ጥንቃቄ በተሞላበት የሚያከናውኑበትን ዕቅድ ማዘጋጀት
- የፕሮጀክት ሰራተኞች እና አመቻቾች ምክረ ሃሳቦች ለራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ማቅረብ የመጨረሻ ውሳኔው የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ይሆናል፡፡

### *የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት እና ሀገራዊ የኮቪድ-19 ድጋፍ ፕሮግራሞች*

- የራስ አገዝ ቡድን አሰራርን የሚሰሩ ድርጅቶች በአከባቢው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ስለሚገኙ የኮቪድ-19 ድጋፍ ፕሮግራሞች መረጃ ሊኖራቸው ይገባል
- ከፕሮግራሞቹ የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተቋማቱን የማስተዋወቅ እና የማመቻቸት ስራዎችን መስራት
- በሂደቱ ህብረቶች እና ጥምረቶችን ከፊት ማምጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር ማገናኘት

### *ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት*

- የራስ አገዝ ቡድን ተቋማትን በኮቪድ-19 ወቅት ድጋፍ ለማድረግ ከመንግስታዊ ተቋማት፣ከግል ተቋማት እና ከሌሎች መንግስታዊ ካልሆን ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል፡፡

### *የራስ አገዝ ተቋማት ተወካዮች እና ተቋማቱ ላይ መረጃ መያዝ*

- በራስ አገዝ ቡድን ስራ ላይ የፕሮጀክት ኦፊሰሮች እና አመቻቾችን ስም ዝርዝር እና ስልክ መዝግቦ መያዝ
- በኮቪድ 19 ወቅት በአካል ተገኝቶ ድጋፍ ማድረግ ባይቻል የራስ አገዝ ተቋማቱን ድጋፍ ለማድረግ  ቢያንስ የተወካዮች ስም ዝርዝር እና ስልክ መዝግቦ መያዝ

## ክፍል 3፤
## ጥንቃቄ የተሞላበት የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ተግባሮች መመሪያ

### *ከራስ አገዝ ቡድኖች፣ህብረት እና ጥምረቶች ከስብሰባ በፊት የሚደረጉ ጥንቃቄዎች*

- ሰላምታ ለመስጠት እጅ መንሳት
- የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ
- በአባላት መካከል ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል ርቀትን መጠበቅ
- ፊት በእጅ አለመንካት

## በራስ አገዝ ቡድን ስብሰባ ወቅት

- የቡድን አባላት ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል ርቀትን ጠብቆ መቀመጥ
- የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ
- አንድ ሰው ብቻ በንፁህ እጆች የቁጠባ ደብተሮችን እና መዝገብን አውጥቶ ይመዝገብ
- በቁጠባ ወቅት፣ገንዘብ መቀበል በንፁህ እጆች በአንድ ሰው ብቻ ይፈፀም
- እስክርቢቶ፣ካልኩሌተር ወይም ሌሎች ዕቃዎችን
- የግል ቁጠባ ደብተር አለመቀባበል

## የራስ አገዝ ቡድን አባላት የንግድ ስራ በሚሰሩበት ወቅት

- የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ
- ገንዘብ እና ሌሎች እቃዎች ከነኩ በኃለ እጅን መታጠብ ወይም በአልኮል ማጽዳት
- ደንበኞችን ሲያስተናግዱ ርቀትን መጠበቅ

## የቡድኖች ሚና

- አባላት ራሳቸወን እና የቤሰባቸውን ንጽህና መጠበቅ
- አባላት ልጆቻቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማሳወቅ

## በህብረቶች ስብሰባ ወቅት

- አባላት ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል ርቀትን ጠብቆ መቀመጥ
- የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ
- አንድ ሰው ብቻ በንፁህ እጆች መዛግብትን መያዝ፣ መጻፍ ንክኪን መቀነስ

## የህብረቶች ሚና

- የራስ አገዝ ቡድን አባላት በኮቪድ-19 ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስተማር
- የራስ አገዝ ቡድን አባላት የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና ፣ የተለያዩ ድጋፎችን የሚያገኙበትን መንገዶች ማመቻቸት
- ኮቪድ19 በተመለከተ የሚወጡ ትክክለኛ መረጃዎችን ለራስ አገዝ ቡድን አባላት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም (ለምሳሌ -በስልክ) ማድረስ

### በጥምረቶች ስብሰባ ወቅት

- አባላት ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል ርቀትን ጠብቆ መቀመጥ
- የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ
- አንድ ሰው ብቻ በንፁህ እጆች መዛግብትን መያዝ፣ መጻፍ ንክኪን መቀነስ

### የጥምረት ሚና

- ለኮቪድ -19 ምላሽ ለመስጠት የተቀመጡ መመሪያዎችን መከተል
- የራስ አገዝ ቡድን አባላት የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና፣ የተለያ ድጋፎችን የሚያገኙበትን መንገዶች ማፈላለግ እና ለአባላት ማሳወቅ
- ኮቪድ19 በተመለከተ የሚወጡ ትክክለኛ መረጃዎችን ለራስ አገዝ ቡድን አባላት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም (ለምሳሌ -በስልክ) ማድረስ

# ክፍል አራት፤
# በራስ አገዝ ቡድን አሰራር ውስጥ መረጃ ልውውጥ

በራስ አገዝ አሰራር ውስጥ የሚገኙ አካላት ኮሳፕ፣የኮሳፕ አባል ድርጅቶች እና የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት መሃል በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የመረጃ ልውውጥ መቀጠል አለበት፡፡

- ኮሳፕ በራስ አገዝ ቡድን አሰራር የሚያስተባበሩ ድርጅቶች የፕሮጀክት ኦፊሰሮች፣ አመቻቾች መረጃ መያዝ ማለትም (ስም እና ስልክ ቁጥር)
- የመረጃ ፍሰትን ለማሰለጥ ፤የራስ አገዝ ቡድን ተቋማት ተወካዮች መረጃ መያዝ ማለትም (ስም እና ስልክ ቁጥር)
- በይነመረብን በመጠቀም በራስ አገዝ ቡድን አሰራር ውስጥ የሚሳተፉ አካላት የልምድ ልውውጥ ማድረግ

Consortium of Self-Help Group Approach Promoters (CoSAP)


OUR ADDRESS

Consortium of Self-Help Group Approach Promoters (CoSAP)

*Lideta Sub City, Woreda 10,*

Behind National Tobacco Enterprise,

P.O.Box 26720-1000; Addis Ababa | Ethiopia

Telephone: +251115525251 | +251(0)118959233; +251(0)930 014 725

E-mail: consortium.shg@gmail.com


**STAY CONNECTED**

www.shgconsortiumeth.org

@Consortium of Self Help Group approach promoters

@CoSAP_Ethiopia

@CoSAP Ethiopia